# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

24



«ወዝ-አደሩ ሶሻሊስት ኢትዮጵያን በደሙና በወዙ ይገነባል»

ሚያዝያ ፲፭ —፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# ኢትዮጵያ የአብዮት ደሴት

በፊውዶ ፋሽስቱ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሀገራችን የተበዘበዘችና የተራቆተች ሀገር ብቻ አልነበረችም ። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ ሆና ብሔራዊ ክብሯና ነፃነቷ ተገፎ የተዋረደችና የተናቀች አገርም ነበረች ። በዚያን ዘመን የዓለም ተራማጆች በሙሉ በተለይ ደግሞ የአፍሪካ ተራማጆች ኢትዮጵያን የኢምፔሪያሊስቶች ሴራ መጠንሰሻ ፤ የዓለም አቀፍ አድኃሪዎች መናኸሪያ ፤ የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ትግል ፀር አድርገው ይቆጥሯት ነበር ። በዚያን ዘመን ማንኛውም በአካባቢ ያለ መንግሥት ከዚህ ከፊውዶ ፋሽስቱ ሥርዓት አንፃር ሲታይ መጠነኛ ተራማጅነት ስለነበረው ይቺ አገር ከአካባቢዋ ጋር ስትነፃፀር የፀረ አብዮት የመጨረሻው ምሽግ ሆና የምትታይበት ጊዜ ነበር ። ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የአካባቢው ገዥ መደቦችና የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ኢትዮጵያን እንደወዳጅ አገር ፤ ጭቆናን በቃኝ ብሎ ገና በገፍ ያልተንቀሳቀሰውን ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ «እንደጨዋ ሕዝብ» ቆጥረው እያሞካሹ አንዳንዴም በፊውዶ ፋሽስቱ ሥርዓት ታፍኖ ለተያዘው ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአዞ ዕንባ እያፈሰሱ ይመጻደቁ እንደነበረ የምናስታውሰው ሐቅ ነው ።

ዛሬ ግን ነገሩ ሁሉ ተገለባብጧል ። ለአድኃሪዎች ምንም ዓይነት ፋታ ሳይሰጥ ሦስት ዓመት ሙሉ እየተንቦገቦገ አገሪቱን ያጥለቀለቃት ሕዝባዊ አብዮት ሰደድ የኢትዮጵያንና የአካባቢዋን ሁኔታ ጨርሶ ለውጦታል ። የኢትዮጵያ ጭቁኖች ባለፉት ሦስት ዓመታት በትግልና በመስዋዕትነት የተቀዳጅዋቸውን ድሎች አንግበው ለአካባቢው ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ የሚያበራ የአብዮት ችቦ ይዘው በጭቁን ሕዝቦች የትግል ጐዳና ላይ አኩሪ የሆነ የግንባር ቀደም ቦታ ይዘዋል ።

ትላንት በአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ትግል ላይ ለሚደረገው ሴራ ሁሉ የነሲ. አይ. ኤ. መናኸሪያ የነበረችው አገራችን ዛሬ የዓለም አቀፍ አድኃሪ ኃይሎች ሊያጠፏት የተነሳሱበት አገር ሆናለች ። ትላንት በፊውዶ ፋሽስት ጨለማ ሥር ታሥሮ የአዞ ዕንባ ይፈስላት የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የጭቆናን ቀንበር አሽቀንጥሮ እየጣለ የገዛ ዕድሉን እጁ ለማስገባት ሲነሳ የአካባቢው አድኃሪ ኃይሎች የጥላቻ ምሳር ማረፊያ ሆነ ። ትላንት የአብዮታቸውና የትግላቸው ፀር አድርገው ይቆጥሯት የነበሩት የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦችና ተራማጅ ኃይሎች ከዚች አብዮታዊት አገር በሚያንፀባርቀው የነፃነት ብርሃን ለትግላቸው አዲስ ተስፋና ሕያው ምሳሌ አገኙ ። ትላንት የፀረ አብዮት መዲና የነበረችው እናት አገራችን ዛሬ በአካባቢዋ ያሉትን «የትላንትና ተራማጆች» አልፋ በመመንጠቋ በለየላቸው አድኃሪና በተራማጅ መሳይ መንግሥታት ተከባ የአብዮት ደሴት ሆናለች ።



በዚህ ሁኔታ የተነሳ በዘይት ብር በናጠጡና የነሱ ቡችሎች በሆኑ ገዥ መደቦች ተከበ የውስጥና የውጭ አድኃሪ ኃይሎችን መደምሰስና አብዮትን ፈር ማስያዝ የዚች አብዮታዊት እናት አገራችን ታሪካዊ ዕጣ ሆኗል ። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ከበባ ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም ። መላው አፍሪካና የአካባቢው አገሮች በኮሎኒያሊዝም ቀንበር ሥር ወድቀው ይማቅቁ በነበሩበት ዘመን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ብቻቸውን አንግበውት የነበረው የነፃነት ችቦ ከዚች ምድር በቅኝ ግዛት ሥር ለወደቁ ሕዝቦች ሁሉ ሲያበራላቸው ቆይቷል ። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ይህንን ታሪካዊ ክብር መጐናጸፍ የቻሉት በዕድል ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን ክብር ላለው ኑሮ ሲሉ አስፈላጊ የሆነውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመቀበል በመዘጋጀታቸውና በመቀበላቸውም ነው ።

ዛሬ ደግሞ ሀገራችን የአብዮት ደሴት ሆና እንደዚሁ ለአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች አንግባ የተነሳችበት ሌላ ምሳሌነት አላት ። በኢምፔሪያሊዝም ቀንበር ሥር ወድቀው ለሚማቅቁ ጭቁን ሕዝቦች የብሔራዊ ነፃነት ችቦ ታበራለች ። በውስጥ አድኃሪ ኃይሎች ተጨቁነው ለታፈኑ ሕዝቦች የሕዝባዊ አብዮታዊ አመፅ ዓርማ ይዛ ተነስታለች ። አዲሱና አብዮታዊው የኢትዮጵያ ትውልድ ለዚህ ታሪክ ለጣለበት አዲስ አደራ ብቁነቱን ለማስመስከር በደሙ ሌላ አኩሪ የታሪክ ምዕራፍ በመጻፍ ላይ ይገኛል ።

በፀረ አብዮት ኃይሎች ተከባ በመዋከብ ላይ የምትገኘው የአብዮት ደሴት የሆነች እናት አገራችን ለዚህ ታሪክ በድጋሚ ለጣለባት የብቸኝነት ጉዞ ብቁ ትሆን አትሆን የዓለም ጭቁን ሕዝቦችና ተራማጅ ኃይሎች አተኩረው ይመለከቷታል ። አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት ብሎ ከዳር እስከዳር የተነሳው አዲስ ትውልድ በሁለት የተያያዙ አቅጣጫዎች በትግሉ ገፍቶ ለሰላም ፤ ለነፃነት ፤ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም ለሚደረገው ዓለም አቀፍ ተጋድሎ የሚጠበቅበትን ድርሻ ከማበርከት ወደኋላ አይልም ።

በመጀመሪያ በኢምፔሪያሊዝም ቀንበር ሥር ወድቀው ብሔራዊ ነፃነታቸውንና ክብራቸውን ለተገፈፉ የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ይቺ አገር በታጋይ ልጆቹዋ ትግልና መስዋዕትነት ላይ ተመርኩዛ የብሔራዊ ክብርና ነፃነት ችቦ ይዛ ትቆማለች ። በዚህም ተጋድሎዋ የዓለም ተራማጅ ኃይሎችና ሶሻሊስት አገሮች ድጋፍ የማይለያት ቢሆንም የእናት አገራችን ብሔራዊ ክብርና ነፃነት ዋስትና ታጋይ ልጆቹዋ ለእናት አገራቸው ያላቸው ፍቅር ፤ ለአብዮታቸው ያላቸው ታማኝነትና የገዛ አገራቸውን በራሳቸው ነፃ ለማውጣት ያላቸው ዝግጁነት ብቻ ነው ።

ሁለተኛ ከዚህ ትግል ጋር በምንም ዓይነት ሳትገነጠል በጭቆና ሥርዓት ሥር ወድቀው ግፍና ብዝበዛ ለሚፈጸምባቸው የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ይቺ አገር በአብዮታውያን ልጆቹዋ ትግ

ሊና መስዋዕትነት የውስጥ አድኃሪ ኃይሎችን ጨርሳ በመደምሰስና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቷን ከግቡ ለማድረስ የአብዮት ችቦ አንስታ ለአካባቢዋ ታበራለች ። ለዚህም ቢሆን የዓለምተራማጅ ኃይሎችና የሶሻሊስት አገሮች ሙሉ ድጋፍ አላት ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን የአብዮታችን ግቡን መምታት ዋስትናው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሁሉ በፊት በራሱ ላይ ተማምኖ ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ የሚያካሂደው ሕዝባዊ አመፅ ብቻ ነው ።

እንግዲህ ታሪክ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጨለማ መንጥቆ አውጥቶ የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ትግል ግንባር ቀደም ያደረጋት አገራችን ብሔራዊ ክብሯንና ነፃነቷን እስከብራ አብዮቷን ከግቡ አድርሳ የዓለም ጭቁን ሕዝቦች የሚጠብቁባትን አስተዋፅኦ ታበረክታለች ። ይህም ትግል ለሚጠይቀው መስዋዕትነት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ካደነቀው ጀግንነቱና የአገር ፍቅር ስሜቱ ሳይቆጥብ ይለግሳል ። በአድኃሪ ኃይሎች ተከበን የአብዮት ደሴት ስንሆን በከበቡን ኃያል አድኃሪ ኃይሎች ፊት ብርክ ይዞን አንንበረከክም ። እነዚህ ጠላቶች ምን ያህል ኃያል ቢሆኑም በጀግናው ፤ በአብዮታዊው በአገር ወዳዱና በታጋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ዞሮ ዞሮ ኢምንት ናቸው ። ክብርና ነፃነት ላለው ኑሮ ቆርጦ ተነስቶ «አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት» ብሏልና ጠላቶቹን ሁሉ ደምስሶ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ክብሩን ሙሉ በሙሉ መጐናጸፉ አብዮቱን ከግቡ ማድረሱ የማይቀር የታሪክ ሐቅ ነው ።

አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት !

ድል የሰፊው ሕዝብ ነው ! ።